# ፀረ-ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 43 ሰኔ 15 /2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገፆች


ማዕከሉ የብልሹ አሰራርና የሙስና ስጋቶችን በመቅረፍ ረገድ ያለውን ሚና ከፍተኛ ነው - ርዕሰ መስተዳድር ጥላሁን ከበደ
ገጽ 3


ኮሚሽኑ ለተቋማት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች በዲጂታል ሀብት ምዝገባ አተገባበር ላይ ስልጠናዊ ግምገማ አካሄደ
ገጽ 4

የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት 50 ሺህ ብር መደለያ የተቀበሉ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ዋሉ
ገጽ 5



የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!


## “መሶብ” የአንድ ማዕከል አገልግሎት የዜጎችን ጊዜ የሚቆጥብ፣ የሙስና ቀዳዳዎችን የሚደፍን እንዲሁም በመንግሥት በኩል የተቋማትን ታማኝነትና ጥንካሬ የሚያጎለብት ነው - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) “ዲጂታል ለልህቀት” በሚል መሪ ቃል በተዘጋጀው ጉባኤ ላይ በመገኘት፣ ከተለያዩ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን በአንድ መድረክ ላይ የሚያጣምረውን እና በአፍሪካ ቀዳሚ የሆነውን የተቀናጀ የዲጂታል አገልግሎት መተግበሪያ በይፋ መርቀው ስራ አስጀምረዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚሁ ጊዜ ባስተላለፉት መልእክት፣ ይህ ታላቅ ስኬት ለሀገራችን ከፍተኛ የኩራት ምንጭ ከመሆኑም በላይ በቴክኖሎጂ የሚመራ እና ዓላማ ተኮር ኢንቨስትመንት ምን ሊያስገኝ እንደሚችል ማረጋገጫ መሆኑን ገልጸዋል::

“መሶብ” የተሰኘው ይኸው የአንድ ማዕከል አገልግሎት ወሳኝ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት



መሆኑን ያብራሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ መተግበሪያው የዜጎችን ጊዜ እንደሚቆጥብ፣ የሙስና ቀዳዳዎችን እንደሚደፍን፣ እንዲሁም በመንግሥት በኩል የተቋማትን ታማኝነትና ጥንካሬ እንደሚያጎለብት አስታውቀዋል:: አያይዘውም ይህ ስኬት ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ ትልሞች ተራ ምኞት ብቻ ሳይሆኑ፣ በራሳችን እጆችና አቅም የምንገነባቸው እውነታዎች መሆናቸውን በግልጽ የሚያሳይ ምስክር መሆኑን አብራርተዋል::ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይህንን ስኬት ይበልጥ በማጠናከር፣ የተገኘውን ልምድና ተሞክሮ ለአፍሪካውያን ወንድሞች እና እህቶች በማካፈል፣ እንዲሁም ከዚህ የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ በቁርጠኝነት ወደፊት መጓዝ እንደሚገባ አገራዊ ጥሪያቸውን አቅርበዋል::

## ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ፒ.ኤች.ዲ) ከኮሪያ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አካሄዱ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ፒ.ኤች.ዲ) ከኮሪያ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (KOIKA) የሥራ ኃላፊዎች ጋር በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ ቀጣይነት ያለው ሥራ በጋራ ለመስራት ውይይት አካሂደዋል:: በውይይቱም በፀረ-ሙስና ህጎች ትግበራ፣ በተቋማት የጥቅም ግጭት መከላከል፣ በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ፣ በሀብት ምዝገባ መረጃ የማጣራት አፈጻጸም፣ በተቋማት ኃላፊዎች የሥነምግባር ኮድ አፈፃፀም፣ በፀረ-ሙስና ትግል ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሰራ ተመላክቷል::

የኮሪያ የሥነምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና ትግል ልምድ ለሀገራችን ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለውና ትግሉን በውጤታማነት ለመምራት እንደሚያግዝ ተጠቁሟል:: እንዲሁም ሙስናን ለመከላከል ዲጂታል አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ የተጠቆመ ሲሆን፣ ይህም የሀገር ውስጥ ኢንቨስትምንትን ለመሳብ አስቻይ ሁኔታ እንደሚፈጥርና ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋጽኦ እንዳለው ተገልጿል: : ኮሚሽኑ እና የኮሪያ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (KOIKA) በትብብር የሚሰሩ ሲሆን፣ በዚህም ለኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በኮሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱ ይታወሳል::

## ኮሚሽኑ የመካከለኛ ዘመን ሀገራዊ የሥነ-ምግባር ግንባታ ስልጠና እና የሙስና መከላከል ጥናት የፋይዳ ግምገማ የባለድርሻ ምክክር መድረክ አካሄደ



የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በመካከለኛ ዘመን ስትራቴጅካዊ ዕቅድ (ከ2016-2018) የበጀት ዓመታት ሀገራዊ የሥነ-ምግባር ግንባታ ሥልጠና እና ሙስና መከላከል ሥራዎች ላይ የግምገማና ምክክር መድረክ አካሂዷል:: በምክክር መድረኩ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣ የፌደራል፣ የክልልና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነሮችና የሥራ ኃላፊዎች፣ የባለድርሻ አካላት ተወካዮች፣



የዘርፍ ፎረም አመራሮችና ረዳት አሰልጣኞች ተሳትፈዋል::

በምክክር መድረኩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ እንደገለጹት፤ ይህ መድረክ በሦስት ዓመታት የፀረ-ሙስና ትግል ሂደቶችን ገምግመን ውጤቶችን የምናስቀጥልበት እና ጉድለቶችን የምናርምበት ነው:: መንግሥት ለፀረ-ሙስና ትግሉ በሰጠው ትኩረት እና ባስቀመጠው የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት በሥነ-ምግባር ግንባታ እና በሙስና መከላከል ላይ የተሠሩ ሥራዎች ቀላል የማይባል ውጤት እንዳመጡ ገልጸዋል::

አሁንም ከሕብረተሰቡ የሚቀርቡ የመልካም አስተዳደር እና የሙስና መከላከል ጥያቄዎችን ለመፍታት መንግሥት በቁርጠኝነት ይሠራል ብለዋል:: በሪፎርሙ እየመጡ ያሉ ተጨባጭ ለውጦችን ከወሬ ባለፈ በመሬት ላይ ያለውን እውነታ መረዳት ያስፈልጋል ያሉት የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው፣ ይሁን እንጂ ቀሪ ሥራዎች ስላሉ በሙስና መከላከል ጥናት የተለዩ የኦዲት እና የግዥ ጉድለቶችን ለማስተካከል እንደ እነዚህ ዓይነት የምክክር መድረኮች አስፈላጊ ናቸው ብለዋል::

በመጨረሻም ባለፉት ሦስት ዓመታት የተመዘገቡ ውጤቶችን ለማስቀጠል በእያንዳንዱ በሚሠሩ ሥራዎች በባለቤት እና በእኔነት መንፈስ መሥራት እንደሚገባ እና በየመዋቅሩ ያሉ አመራር እና ሠራተኞች አቅማቸውን በመገንባት ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተውና ተናበው መሥራት እንደሚጠበቅ በማመላከት ሐሳባቸውን ቋጭተዋል::

ወደ ገጽ 2 የዞረ

## ኮሚሽኑ የመካከለኛ ዘመን ሀገራዊ የሥነ-ምግባር ግንባታ... ከገጽ 1 የዞረ





የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ፒ.ኤች.ዲ) በበኩላቸው ባለፉት ሦስት ዓመታት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ በስታንዳርድ ላይ የተመሠረተ ዘርፍ ተኮር የሥነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ጥናቶች ተካሂደዋል ብለዋል። አያይዘውም ጥናቶቹም በየዘርፉ የተዘረጉ አሠራሮች ምን ያህል ለሙስና የተጋለጡ ናቸው የሚለውን ያሳዩ መሆናቸውን እና ጥናቶቹ ለሚመለከታቸው የዘርፍና ተቋማት ኃላፊዎች ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው መሆናቸውን አስረድተዋል።

በርካታ ተቋማት የጥናቱን ውጤት ተቀብለው ተግባራዊ ለማድረግ እና ለግልጽነትና ተጠያቂነት ብቁ መሆናቸውን ገልጸዋል። እንደ ሀገር በሙስና መከላከል ጥናት እና በሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ማጣራት ያገኘናቸውን ግኝቶች አደራጅተን የሙስና አዝማሚያ የታየባቸውን ለይተን ለሚመለከተው አካል እናቀርባለን ያሉት ኮሚሽነሩ፣ ይህ የውይይት መድረክ ሲዘጋጅም በጥናቶቹ መነሻ ላይ ሐሳብ ለማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል የጉባኤው አስፈላጊነት የመካከለኛ ዘመን የሥነ-ምግባር ግንባታ ሥልጠናዎች ምን ያህል ውጤታማና ችግር ፈች ናቸው የሚለውን ለመገምገም የተዘጋጀ መሆኑንም ገልጸዋል። አክለውም ሀገራዊ የሥነ-ምግባር ግንባታ ሥራው ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮችን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፤ የሥልጠና ጥራትና ተገቢነትን ማረጋገጥ፣ ዘርፍ ተኮር የሥልጠና ዘዴን መከተል እና ተደራሽነትን ማስፋት መሆናቸውን አብራርተዋል።

በመድረኩ የቀረበው ሰነድ ሥልጠናውን ውጤታማነት በሚመለከት፣ አመራሮች እና ሠራተኞች ሥነ-ምግባራዊ ሆነው እየመሩ ነው ወይ፣ ተቋማት አሠራራቸውን ግልጽ ከማድረግ አንጻር ምን ደረጃ ላይ ናቸው፣ የሀብት አስተዳደር ተሻሽሏል ወይ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመዳሰስ የተደረገ ጥናት መሆናቸውን ገልጸዋል። የሥልጠናውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ከኮሚሽኑ በተጨማሪ በገለልተኛ አካል እየተጠና መሆኑን የተናገሩት ኮሚሽነሩ በቀጣይም ዘርፍ ተኮር የሥነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎች የበለጠ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ጠቁመዋል፡፡

የሁለቱም ስትራቴጅክ ጉዳዮች የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በኮሚሽኑ መሪ ሥራ አስፈጻሚዎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ በውይይቱም ከተሳታፊዎች በርካታ ሐሳቦች ተነስተዋል። ከተነሱ ሐሳቦችና አስተያየቶች መካከልም በሙስና መከላከልም ሆነ በሥነ-ምግባር ግንባታው ሂደት የተሠሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸው፤ በመከላከል ሥራው በርካታ የሕዝብ ሀብት ማዳን መቻሉ፤ ጥናቶቹ በየዘርፉ ለሙስና አጋላጭ ምክንያቶችን ለመለየት ያስቻሉ መሆናቸው፤ በጥናቶቹ ምክረ-ሐሳብ መነሻነት አሠራሮችን በቴክኖሎጂ ለማዘመን ዕድል የሚፈጥሩ መሆናቸው፤ የጥናት ግኝቶች ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጡ ግኝቶቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ አስገዳጅ ሕግ ቢወጣ እና ተግባራዊ በማያደርጉት ላይ ተጠያቂነት ቢረጋገጥ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት፣ ለማጣራት በሚቀርቡ ጥቆማዎች ላይ መረጃና ማስረጃ የማቅረብ ውስንነት መኖሩ፤ ሥልጠናዎችን ተደራሽ ለማድረግ ከፊት ለፊት በተጨማሪ በበየነ-መረብ ጭምር ቢሰጥ፤ ሥልጠናዎች የክልል መከታተያ ክፍሎችንም ቢያካተት፤ አሰልጣኞች ከከፍተኛ ትምህርት ምሁራን በተጨማሪ የውስጥ አቅምንም መጠቀም ቢቻል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ የሰጡት የኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው እንደገለጹት፤ ሦስቱ የፀረ-ሙስና መሠረታዊ ስልቶች የሚባሉት ማስተማር፣ መከላከል እና ሕግ ማስከበር ናቸው።

በየዘርፎቹ በተከናወኑ የሙስና መከላከል ጥናቶች ላይ ከሚመለከታቸው የዘርፍ አመራሮችና ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተካሂዶ አብዛኞቹ አመራሮች የጥናቱን ግኝቶች እንደተቀበሉ ገልፀዋል። አያይዘውም ለጥናቶቹ ምክረ-ሐሳቦች የትግበራ የድርጊት መርሃ-ግብር ወጥቶላቸው ተግባራዊ እየተደረጉ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ምክትል ኮሚሽነሩ አክለውም በኮሚሽኑ አዋጅ 1236/2013 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በግልጽ በተቀመጠው መሠረት ኮሚሽኑ ለሙስናና ብልሹ አሠራር የተጋለጡ አሠራሮችን በማጥናት የማስተካከል እና ሙስና ለመፈጸም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነ ሲጠረጥር ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሂደቱን በማቋረጥ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ የማድረግ ሥልጣን አለው ብለዋል፡፡

በዚህም መነሻነት ባለፉት ሦስት ዓመታት በርካታ ጥናቶች መከናወናቸውን ገልጸው፣ ጥናቶቹም በመረጃና ማስረጃ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውንም ተናግረዋል። ሙስና የአመለካከት እና የአስተሳሰብ ጉዳይ ነው ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ ሙስናን ለመከላከል ሁሉንም አቅሞች አቀናጅቶ መጠቀም እና ሦስቱንም የመንግሥት አካላት ተሳትፎ በእኩል መጠን ማሳደግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።



የኮሚሽኑ የሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው የቀረበው የሥልጠና ሰነድ በሦስት ዓመታት ውስጥ የተሠሩ የሥልጠና ጥራትና ተገቢነትን ለማንጸባረቅ እና ሥልጠናው ምን ውጤት አመጣ የሚለውን ለመገምገም የተዘጋጀ ነው ብለዋል፡፡ የሥልጠና ውጤታማነት የሚታወቀው ዛሬ አሰልጥነን ነገ ውጤት መጠበቅ ሳይሆን በጊዜ ሂደት በሚመጣ የአስተሳሰብ እና የአመለካከት ለውጥ መሆኑንም አንስተዋል። የሥልጠና ጥራትና ተገቢነት እንዲሁም ውጤታማነት መለኪያው አንዱ ተደራሽነትን ማስፋት መሆኑን የተናገሩት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ በ2016 በጀት ዓመት 4 ሺህ የነበረውን የሥልጠና ተደራሽነት በ2017 በጀት ዓመት ወደ 75 ሺህ ከፍ ማድረግ ተችሏል ብለዋል። የበለጠ ተደራሽነትን ለማስፋት ሥልጠናዎች ተቀርጸው በኮሚሽኑ የሚዲያ አማራጮች ጭምር በመልቀቅ ለብዙኃኑ ተደራሽ መደረጉንም አስረድተዋል።

የአሰልጣኝ ምልመላና መረጣን በሚመለከት በ2017 በጀት ዓመት መስፈርት በማዘጋጀት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሁራንን በመመልመል ሲሰጥ የቆየ ሲሆን፣ በ2018 በጀት ዓመት ደግሞ ከከፍተኛ ትምህርት ምሁራን በተጨማሪ ከተቋማት መከታተያ ክፍሎች ረዳት አሰልጣኞችን የአሰልጣኞች ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የአሰልጣኞቹን ብቃት ለማሳደግ በድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ጭምር በማሳተፍ ልምድና ተሞክሮ እንዲቀስሙ መደረጉንም ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ሥልጠናው ዘርፍ ተኮር ስለነበር ውጤት አምጥቷል፤ ተቋም ተኮር ብናደርገው ደግሞ የበለጠ ውጤት ያመጣል ያሉ ሲሆን፤ በመጨረሻም ከዚህ ያለው አካል የሥነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከሉ ሰራዊት ስለሆነ በባለቤት እና በያገባኛል መንፈስ በትጋት ሊረባረብ ይገባል፤ በየደረጃው ያለው አመራርና ሠራተኞች በጥሩ ሥነ-ምግባር አርአያ ሆነው መሥራት ይኖርባቸዋል ብለዋል።



## ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ትውልድን የሚያንፁ ትምህርት ቤቶች ድርሻቸው የላቀ መሆኑ ተገለጸ





የአዲስ አበባ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን "ሥነ-ምግባር ያሸልማል" በሚል መሪ ሃሳብ ከተማ አቀፍ የተማሪዎች የጥያቄና መልስ ውድድር አካሂዷል:: በዚሁ ወቅት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ፤ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ትውልድን የሚያንጹ ትምህርት ቤቶች ድርሻቸው የላቀ መሆኑን ገልፀዋል:: በአዲስ አበባ ምክር ቤት የፍትህና መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ በላይ ደጀን በበኩላቸው፤ ሙስናን ለመከላከል ተከታታይነት ያላቸው ስራዎች ተሰርተዋል:: አሰራሮችን ዲጂታል ማድረግ መጀመሩ ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ የላቀ ድርሻ አለው:: ይህን መሰል መድረክ ሀገርን የሚያሻግርና ሌብነትን የሚፀየፍ ትውልድ ለመፍጠር ያስችላልም ብለዋል::

በ2ተኛው ከተማ ዓቀፍ የሥነምግባር ጥያቄና መልስ ውድድሩ በከተማው በየደረጃው ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተወጣጡ በሥነምግባራቸው የተመሰገኑ ውጤታማ ተማሪዎች ተሳትፈዋል:: ተማሪዎቹ በየክፍለ ከተማቸው የተደረጉ የተለያዩ ውድድሮችን በበላይነት በማጠናቀቅ ለመጨረሻው ውድድር የበቁ መሆናቸው ተጠቁሟል:: ውድድሩ በተማሪዎች ዘንድ መልካም ሥነምግባርን ለማስረጽና የፀረ-ሙስና ትግሉን በትውልድ ግንባታ ለማገዝ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው:: በጥያቄና መልስ ውድድሩ አሸናፊ ለሆኑ ተማሪዎች እንዲሁም ሥነምግባር ያሸልማል በሚል መሪ ሀሳብ በየአመቱ በሥነምግባራቸው አርአያ ለሆኑ ተማሪዎች እያደረገው የሚገኘው የእውቅናና ልዩ ልዩ ሽልማቶች ተበርክተዋል::



## ማዕከሉ የብልሹ አሰራርና የሙስና ስጋቶችን በመቅረፍ ረገድ ያለውን ሚና ከፍተኛ ነው - ርዕሰ መስተዳድር ጥላሁን ከበደ






በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የአርባምንጭ መሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከል ምረቃ ላይ የተገኙት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ ማዕከሉ መጀመሩ በክልሉ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነው ብለዋል:: «መሶብ» የአንድ ማዕከል አገልግሎት በተበታተነ መልኩና በባህላዊ አሰራር ሲሰጡ የነበሩ በርካታ የመንግስት አገልግሎቶችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ በማስደገፍ በአንድ ጣሪያ ስር የሚያስተሳስር በመሆኑ፣ ለዘመናት ህብረተሰቡን ሲያማርሩ የነበሩ የቢሮክራሲ ማነቆዎችን ሙሉ በሙሉ እንደሚፈታ ተናግረዋል::

ይህ ማዕከል ዜጎች ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና አላስፈላጊ ወጪያቸውን እንዲቆጥቡ ያደርጋል:: አገልግሎቱ የመንግስትን አገልግሎት ተደራሽነትና ቀልጣፋነት ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር የህዝብን እርካታ እንደሚያረጋግጥ ያብራሩ ሲሆን፣ ማዕከሉ የብልሹ አሰራርና የሙስና ስጋቶችን በመቅረፍ ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑንም አብራርተዋል:: የ«መሶብ» ሥርዓት ሙሉ በሙሉ በዲጂታል መሠረተ ልማትና በቴክኖሎጂ የተደገፈ በመሆኑ፣ የአገልግሎት ሰጪና የነዋሪዎችን ቀጥተኛ ንክኪ በመቀነስ የአገልግሎት አሰጣጡን ግልጽ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበትና ከሙስና የጸዳ እንደሚያደርገውም ርዕሰ መስተዳድሩ አመላክተዋል::

ዘመናዊ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት መዘርጋቱ ብቻውን በቂ እንዳልሆነ በመግለጽ፣ በማዕከሉ የሚመደቡ አመራሮችና ባለሙያዎች የህዝብ አገልጋይነት ስሜትን በተግባር ሊያሳዩ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበው፤ ይህንን የተቀናጀ አሰራር በላቀ የኃላፊነት ስሜትና በታማኝነት በመምራት የክልሉን ነዋሪዎች የዘመናት የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በዘላቂነት መመለስ እንደሚገባ አሳስበዋል::

የኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ወ/ሮ አልማዝ መሰለ በበኩላቸው÷ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ራዕይ ከማሳካት አንጻር እስካሁን 51 የ'MESOB' አንድ ማዕከላት በ11 ክልሎችና በ2ቱ ከተማ መስተዳድሮች ተመርቀው ወደ ስራ የገቡ ሲሆን፣ ዛሬ የሚመረቀው የአርባምንጭ ማዕከል ሲጨመር ቁጥሩን 52 እንደሚደርስ ገልፀዋል:: በክልሉ ከወላይታ ሶዶ ማዕከል ቀጥሎ የአርባምንጭ መሶብ 2ኛው ወደ አገልግሎት የገባ ማዕከል ሲሆን፣ ይህም ሃገራችን አገልግሎቶችን ተደራሽ እና ግልጽ ከማድረግ አንጻር አንድ ደረጃ ከፍ ያደርጋታል ነው ያሉት::

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቃሬ ይህ ማዕከል የዲጂታል ሕልም ፍቺ ነው ያሉ ሲሆን፣ መንግስት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የገባውን ቃል መተግበሩን የሚያሳይ ምስክር መሆኑን አስገንዝበዋል:: የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አበባየሁ ታደሰ (ዶ/ር) በአርባ ምንጭ መሶብ የአንድ ማዕከል አራት የፌደራል እና አምስት የክልሉ ቢሮዎች 32 አገልግሎቶች እንደሚሰጡ ገልፀው፤ ከዚህ በፊት ዜጎች የሚገጥማቸውን እንግልት በጥራትና ፍጥነት የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል::

## የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ውይይት አደረጉ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ውይይት አድርገዋል:

: ውይይቱ የ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ በሰላም መጠናቀቁን አስመልክቶ ከቅድመ ምርጫ ጀምሮ የነበሩ ጠንካራ ጎኖችንና ክፍተቶችን ለመገምገም ነው:

:በውይይቱ ጠንካራ ተቋምና ጠንካራ መንግስት ለመገንባት እንዲሁም የተቋምን የአሰራር ስርዓት ለማሳደግ ምርጫ አስፈላጊ እንደሆነ ተመላክቷል:



: በመድረኩ የቅድመና ድህረ ምርጫ የሚያመላክት ሰነድ የቀረበ ሲሆን፣ ከተሳታፊዎች ሀሳብ፣ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ቀርበው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።



# ኮሚሽኑ ለተቋማት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች በዲጂታል ሀብት ምዝገባ አተገባበር ላይ ስልጠናዊ ግምገማ አካሄደ





የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለተቋማት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች በዲጂታል ሀብት ምዝገባ አተገባበር ላይ ተግባር ተኮር ስልጠናዊ ግምገማ አካሂዷል፡፡ የስልጠናው ዓላማ የዲጂታል ሀብት ምዝገባ አተገባበር ምን ላይ እንዳለ በመገምገም ያጋጠሙ ችግሮችን ለመለየት እና የቀጣይ ውጤታማነቱን አጠናክሮ ለማስቀጠል ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ በመድረኩ ንግግር ያደረጉት በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቱ አስፋው ዲጂታል የሀብት ምዝገባ ስርዓት በከፍተኛ ሁኔታ እየተተገበረ ያለና ውጤታማ የሆነ ስርዓት ነው፡፡ በዚህም የተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሀብታቸውን በዲጂታል ስርዓት እያስመዘገቡ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ሥርዓት ሙስናን ለመከላከል አንዱ መንገድ ነው ያሉት ም/ኮሚሽነሩ ይህን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግና አቅሙን ለማሻሻል ሲስተሙን ወደ ክላውድ ማሳደግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡ በኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው የሀብት ምዝገባ ሥራ በባህሪው አስቸጋሪ በመሆኑ ቴክኖሎጂን መጠቀም ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ደግሞ የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ስርዓት ትልቁ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡ አክለውም ሀብታቸውን ማስመዝገብ ያለባቸው የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሁሉ ሥርዓቱን ተጠቅመው እንዲያስመዘግቡ ግንዛቤ መፍጠሩ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሠራት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡ የዲጂታል የሀብት ምዝገባ ስርዓቱን ውጤታማነቱን ለማስቀጠል ምዝገባውን በካላንደር መምራት የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል ያሉት ደግሞ በኮሚሽኑ የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት መከላከል መሪ ሥራ አስፈጻሚ ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር ናቸው፡፡



በመድረኩ በበጀት ዓመቱ የተቋማት የዲጂታል ሀብት ምዝገባ አፈጻጸም ሪፖርት ቀርቦ ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ በሪፖርቱ ከ128 ሺህ በላይ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሀብታቸውን በዲጂታል ሥርዓቱ እንዳስመዘገቡም ተገልጿል፡፡ ከእነዚህ ወስጥ ከዕቅዳቸው በላይ የሰሩ ተቋማት እንዳሉ ሁሉ ከዕቅድ በታች የሰሩ በመኖራቸው ለምን ወደኋላ ቀሩ የሚለውን ማየት እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፡፡ በመድረኩ በዲጂታል ሥርዓቱ ላይ እስካሁን ያጋጠሙ ችግሮችን በየጊዜው በመለየት መፍታት መቻሉም ተመላክቷል፡፡ በስልጠና መድረኩ የዘርፎችና ተጠሪ ተቋማት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች የተገኙ ሲሆን፤ ከተሳታፊዎች ጥያቄ፣ ሀሳብና አስተያየቶች ተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡





# የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት ነዋሪዎችን ለዓመታት ሲያማርር ከኖረው የአገልግሎት አሰጣጥ እንግልትና ከብልሹ አሠራር የሚታደግ ነው - ከንቲባ አዳነች አቤቤ





የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በይፋ የመረቁት የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት ነዋሪዎችን ለዓመታት ሲያማርር ከኖረው የአገልግሎት አሰጣጥ እንግልትና ከብልሹ አሠራር የሚታደግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከንቲባ አዳነች በማዕከሉ የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር፤ የኮልፌ ነዋሪዎችን ከአገልግሎት አሰጣጥ እንግልትና ከሙስና የሚታደገው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት በይፋ ሥራ መጀመሩን አብስረዋል፡፡ ይህ ዘመናዊ የዲጂታል ማዕከል ለአንድ ወቅት ብቻ ሳይሆን፣ የረጅም ጊዜ የሀገር ግንባታን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተገነባ መሆኑን የጠቆሙት ከንቲባዋ፤ ነዋሪዎች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚደርስባቸውን ውጣ ውረድ በማስቀረት፣ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ሳያባክኑ የፈለጉትን አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል ብለዋል፡፡

በከተማዋ በርካታ የልማት ሥራዎች ቢሰሩም፣ አሁንም ድረስ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚታዩትን እንደ ፈጣን አገልግሎት አለመስጠት፣ እንግልት እና የእጅ መንሻ (ጉቦ) ጥያቄዎችን ከመዋቅሩ ውስጥ መንጭቆ ለማውጣት ማዕከሉ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ነዋሪዎች ፈጣን፣ ቀልጣፋና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ያለምንም ጉቦ ማግኘት የሚችሉበትን አስተማማኝ ሥርዓት ይፈጥራል ብለዋል፡፡ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የተጀመረው ይህ የዲጂታላይዜሽን ንቅናቄ በዚህ ብቻ እንደማያበቃ የገለጹት ከንቲባ አዳነች፣ ሦስት ተመሳሳይ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል አገልግሎት የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ተጠናቀው ለሕዝብ አገልግሎት ክፍት እንደሚሆኑ አስተውቀዋል፡፡



## የመሶብ አገልግሎት ብልሹ አሰራርን በማስቀረት ዘመናዊ አገልግሎት ለመስጠት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ ተገለጸ



በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሆሳዕና ከተማ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት በርዕሰ መስተዳድር እንዳሻው ጣሰው (ዶ/ር) ተመርቆ ሥራ ጀምሯል:: ርዕሰ መስተዳድሩ በዚህ ወቅት እንዳሉት በክልሉ የማዕከሉን ተደራሽነት በማስፋት መንግስታዊ አገልግሎቶችን በጥራትና



በፍጥነት ለመስጠት የተጀመሩ ተግባራት ይጠናከራሉ:: መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የተለያዩ አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል በማቅረብ የማህበረሰቡን እንግልት በማስቀረት በኩል ያለው አስተዋጽኦ ጉልህ መሆኑንም ተናግረዋል:: ማዕከሉ ዜጎች መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚገጥማቸውን ችግር እንደሚያስቀርም አመልክተዋል:: በመሆኑም በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ከተሞች ማዕከላቱ ተገንብተው ለአገልግሎት እንዲበቁ በክልሉ መንግስት በኩል ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል::

የሀድያ ዞን ዋና አስተዳዳሪ




ማቲዎስ አኒዮ በበኩላቸው መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ብልሹ አሰራርን በማስቀረት ለማህበረሰቡ ፈጣን፣ ዘመናዊ አገልግሎት ለመስጠት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል:: ይህ ተመርቆ ለአገልግሎት የበቃው የሆሳዕና ከተማ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ገቢን በአግባቡ በመሰባሰብ ለህዝብ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ጉልህ ጠቀሜታ እንዳለው ገልፀዋል::

## የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ በቤተሰብ እና ማህበራዊ ተቋማት አማካኝነት ለማጎልበት በትብብር ለመሥራት የሚያስችል ምክክር ከወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ አመራሮች ጋር ተደርጓል




የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ አመራሮች ጋር ምክክር አካሂዷል:: በምክክር መድረኩ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ በቤተሰብ እና ማህበራዊ ተቋማት አማካኝነት ለማጎልበት በትብብር መሥራት እንደሚያስፈልግ ውይይት ተደርጓል::


ኮሚሽኑ አገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል ውጤታማ እና ዘላቂ እንዲሆን በትኩረት ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ነው:: በዚህ ወሳኝ አገራዊ አጀንዳ በርካታ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉ ቢሆንም፣ በቀጣይ በትብብር የሚመራበት የአሰራር ሥርዓት እየተዘረጋ ይገኛል:: ትውልዱን በሥነምግባር ማነጽ ከሥር መሠረቱ መሆን እንዳለበት እና ቤተሰብ እንዲሁም ቅድመ-መደበኛ እና መደበኛ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ከተለመደው የዕውቀት እና ክህሎት ግንባታ ባሻገር የመልካም ባህሪ ግንባታ በአርዓያነት የሚፈጽሙበት ተገማች አገራዊ የአሰራር ሥርዓት ማጠናከር የትብብሩ ትኩረት ጉዳይ እንደሆነ በውይይቱ ተመላክቷል::

## የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት 50 ሺህ ብር መደለያ የተቀበሉ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ዋሉ

ግለሰቦቹ የወንጀል ድርጊቱን የፈፀሙት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ህንፃ ውስጥ ነው:: ዘነበ ንጉሴ የተባለው ግለሠብ በጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ የህንፃ መጠቀሚያ ባለሙያ ሲሆን፣ የግል ተበዳይ የግንባታ ፍቃድ ለማውጣት







100 ሺህ ብር ተጠይቀው በድርድር 50 ሺህ ብር ይዘው እንዲመጡ ተስማምተዋል:: የግል ተበዳይ የደረሰባቸውን በደል ለክፍለ ከተማው ፖሊስ የወንጀል መከላከል መምሪያ በሰጡት ጥቆማ ተጠርጣሪው በክትትል አባሎች ገንዘቡን ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተይዟል::

ከጉዳዩ ጋር ተሳትፎ የነበረው በክፍለ ከተማው የግንባታ ፈቃድ የመጠቀሚያ ፈቃድ ባለሙያ የሆነው አድምቀው ውቤ የተባለው ግለሰብ የግል ተበዳይን ጉቦ ካልከፈልክ አገልግሎት እንደማይሰጠው በመንገርና ለአንድ ወር በማጉላላት 50 ሺህ ብሩን እንዲሰጥ በማድረግ የማግባባት ስራ ሲሰራ እንደነበር ፖሊስ ገልጿል:: ህብረተሰቡ መብቱን በገንዘብ መግዛት እንደሌለበት ያሳሰበው የአዲስ አበባ ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ መሰል የወንጀል ድርጊት ሲፈጸም ጉዳዩን በእጅ ስልኮች የዜጎች ተሳትፎ መተግበሪያ (citizen engagement application) በመጠቀም መረጃ መስጠት ይቻላል::



# ቆይታ

**የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ሥራወቹን በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ ነው:: ስለሆነም የኮሚሽኑ የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ክፍል በየ15 ቀናት ውስጥ የተከናወኑ የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎችን በተለያዩ የጋዜጣዋ አምዶች ከፋፍሎ በማዘጋዘጀት "በዲጅታል ጋዜጣ' አማካኝነት ለህዝቡ ተደራሽ የማድረግ ስራ እየሰራ ይገኛል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ የኮሚሽኑ የፀረ-ሙስና ጋዜጣ የሙስና ሥጋት ሁኔታዎችን እና የመከላከያ ስልቶችን በሚመለከት ዘገባ ለመስራት ከሙስና መከላከል ጥናት መሪ ስራ አስፈጻሚ ጋር አጭር ቆይታ አድርጋለች::**



ገዛኸኝ ጋሻው በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ጥናት መሪ ሥራ አሰፈፃሚ

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** በመጀመሪያ ለቃለ-መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ እናመሰግናለን፣ በመቀጠል ራስዎን እና ኃላፊነትዎን ለአንባቢያን ያስተዋውቁ፤

*መሪ ሥራ አስፈጻሚው:- አቶ ገዛኸኝ ጋሻው እባላለሁ:: በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ጥናት መሪ ሥራ አሰፈፃሚ ነኝ::*

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** ሙስና መከላከል ጥናት ምንነት እና ጥናቱን ለማድረግ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ወይም የሙስና ስጋት መኖሩን የሚያመለክቱ ምልክቶች (Red Flags) ምን ምን ናቸው?

**አቶ ገዛኸኝ ጋሻው:-** የሙስና መከላከል ጥናት በአንድ ተቋም ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ ወይም ግልፅነት የጎደላቸው ወይም የአሰራር ክፍተት ያለባቸው አሰራሮችን መረጃና ማስረጃ ላይ በመመስረት የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ የሚካሄድ ጥናት ነው:: የሙስና መከላከል ጥናት ለማካሄድ የሙስና ስጋት መኖሩን የሚያመለክቱ ጉዳዮች መገለጫ በርካታ ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ዋና ዋናዎቹ በስራ አካባቢዎች በተለያዩ ቦታዎች በተደጋጋሚ የሚፈጠሩ የተጋላጭነት ማሳያዎች ናቸው::

ይኸውም የንብረት አስተዳደር፣ የተለያዩ የግንባታ ፕሮጀክቶች ግዥ አፈጻጸም፣ የውል አስተዳደር፣ የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ችግር፣ የግብር አተማመንና አወሳሰን፣ የትምህርት ማስረጃ፣ የመንጃ ፈቃድ፣ የህክምና ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ፣ የብድር አፈቃቀድና አመላለስ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቃት ማረጋገጥ እና የንብረት አያያዝና አወጋገድ ስርዓት እንደማሳያ ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው::

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** ኮሚሽኑ ባለፉት የመካከለኛ ዘመን የሙስና መከላከል ስትራቴጅክ እቅድ ዓመታት ያከናወናቸው ሀገራዊ የሙስና መከላከል ጥናቶች ካሉ እና ሙስናን በመከላከል ረገድ ለዘርፎች ወይም ተቋማት ያበረከቱት አስተዋፅኦ ምን እንደሆነ ያብራሩልን?

**አቶ ገዛኸኝ ጋሻው:-** እንደሚታወቀው የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የኮሚሽኑን ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሠረት በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስና መከላከል ጥናቶችን ለማካሄድ የሙስና መከላከል ተግባራትን ለመከናወን ስልጣንና ተግባር የተሰጠው ተቋም ነው::

በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናቶች ለማካሄድ ዘርፍ ተኮር ስትራቴጂዎችን ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ ውለው በርካታ የሙስና መከላከል ጥናቶች ተደርገዋል:: ከዚህ አኳያ በ2014/2015 በጀት ዓመት በ25 ዘርፎችና ተጠሪ ተቋማት የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ጥናቶች እና ቁልፍ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ዝርዝር ጥናቶችን ማካሄድ ተችሏል:: ከእነዚህ መካከል የውጭ ሀገር ስራ ስምሪት አሰራር ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያለው ተጋላጭነት፣ የገቢ አሰባሰብና አወሳሰን፣ የጉሙሩክ እና ኮንትሮባንድ አስተዳደር የአሰራር ስርዓት፣ የመንግስት ግዥ ግልፅነት፣ የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦት፣ የመንገድ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የውል አስተዳደር ግልፅነት፣ የመስኖ ግድብ ፕሮጀክቶች የውል አስተዳደር ስርዓት ግልፅነት ጥናቶች ተጠኚ ተቋማቱ የአሰራር፣ የአደረጃጀት እና የህግ ማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ የአሰራር ስርዓታቸውን ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖረው አስችሏል ማለት ይቻላል::

ከዚህ በተጨማሪ መሰል የሙስና መከላከል ጥናቶች በክልልና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ተደርገዋል:: ኮሚሽኑም በሕግ በተሰጠው የሕግ ኃላፊነት መሰረት ለክልልና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ቴክኒካዊ ድጋፍ በማድረግ ጥናቶች ውጤት እንዲኖራቸው ማድረግ ችሏል::

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችን ለመለየት እና ለመከላከል የምትጠቀሙባቸው ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

**አቶ ገዛኸኝ ጋሻው:-** የሙስና መከላከል ጥናቶች ከመከናወናቸው በፊት ከላይ እንደተመለከተው በመንግስት እና ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ወይም የሚስተዋሉ ተጋላጭ አሰራሮች የትኞቹ ናቸው? ጥናትስ ቢደረግ ትርጉም ባለው መልኩ ችግር ፈቺ ሊሆን የሚችለው በየትኛው ዘርፍና ርእሰ ጉዳይ ቢጠና የተሻለ ይሆናል የሚለው ዋነኛ ጉዳይ ሲሆን፣ የሙስና ስጋቶችን ለመከላከል እና ለመለየት:-

1. ተቋማት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ባህሪ አንጻር፣

አንዳንድ ተግባራት በባህሪያቸው ለሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶች የተጋለጡ ሲሆኑ፣ አንዳንዶች ደግሞ በንጽጽር ሲታዩ ተደጋጋሚ የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶች የማይፈጸሙባቸው ሆነው ይገኛሉ::

2. ከሚንቀሳቀሰው የገንዘብ መጠን፣

ሙስና በአብዛኛው ሊያመጣ የሚችለውን ትርፍና ኪሳራ በማመዛዘን የሚከናወን የወንጀል ድርጊት እንደመሆኑ ከፍተኛ ገንዘብ የሚንቀሳቀስባቸው አሰራሮች የበለጠ ፈጻሚዎችን ለወንጀሉ የሚያነሳሱ በመሆናቸው የተጋላጭነታቸው ደረጃ ይጨምራል::

3. ከቁጥጥር ስርዓት፣

በዘርፍ (በተቋማት) ውስጥ ያለው የቁጥጥር ስርአት ደረጃ ፈጻሚዎችን እንዲታቀቡ በማድረግ ወይም እንዲደፋፈሩ ለማድረግ ወሳኝነት ያለው በመሆኑ በሙስና

ተጋላጭነት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

አንድ ተቋም አሰራሩ በግልጽ የተቀመጠ፣ ተጠያቂነት ያለበትና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ያለው ሲሆን፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊኖረው የሚችለው ተጋላጭነት የሚቀንስ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ቁጥጥርን ብቻ ማዕከል በማድረግ በየደረጃው ያሉ የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞችን በሚከናወኑ ስራዎች ላይ አሳታፊ የማይሆን ከሆነ ተቋሙ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ በሚፈጠር መሰናክል ምክንያት የሙስና ተጋላጭነት ደረጃው ሊጨምር ይችላል፡፡

በመሆኑም ማንኛውም የተቋም አሰራር ተገቢው የሙስና መከላከል ስራ ካልተሰራለት ለሙስና ሊጋለጥ የሚችል ቢሆንም አንዳንድ የስራ ሂደቶች ደግሞ ካላቸው የስራ ባህሪ አንጻር የበለጠ ተጋላጭ ሆነው እንደሚገኙ መረጃዎች የሚያሳዩ በመሆኑ ሙስናን ብልሹ አሰራርን በመከላከል የተጋላጭነት ስጋትን ማስወገድ የሚገባ ይሆናል፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በአንድ ዘርፍ/ተቋም ውስጥ ያሉ የስራ ክፍሎች ለሙስና ተጋላጭ መሆናቸው እንዴት ይገመግማሉ ወይም አመላካች ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?

**አቶ ገዛኸኝ ጋሻው፡-** አንድ ዘርፍ ወይም ሚኒስቴር መ/ቤት እና ተጠሪ ተቋማቱ በሕግ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ኃላፊነቱን ለማሳካት ግዥዎችን ሊፈፅም፣ ግዥዎችን ተከትሎ ውሎችን ሊያስተዳደር፣ ብድር ሊሰጥ፣ ገቢ ሊወስን፤ ሊሰበስብ፣ የግብር ከፋዮችን ግብር ኦዲት ሊያደርግ፣ የኮንስትራክሽን ፈቃድ፣ የተለያዩ የሙያ ፈቃዶችን ሊሰጥ፣ ሊያድስ፣ የስራ ዕድል ስምሪት ሊሰጥና ሊቆጣጠር ወዘተ ይችላል፡፡ እነዚህን ተግባርና ኃላፊነት በሚወጣበት ወቅት የሚያከናውናቸው ተግባራት ሂደት ግልፅነት፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ መሆናቸው፣ የቅሬታ አፈታት ስርዓት አለመኖር፣ ቢኖርም ግልፅነት የሌለው ሂደት ከሆነ፣ የአሳታፊነት ሁኔታው እና የመሳሰሉት ጉዳዮች እንደምክንያት ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የሙስና መከላከል ጥናት ሪፖርት ውስጥ መካተት ያለባቸው ዋና ዋና ክፍሎች ምንድን ናቸው?

አቶ ገዛኸኝ ጋሻው፡- የሙስና መካለክል ጥናት ሪፖርት የተለያዩ ነጥቦችን የሚያካትት ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የጥናቱ ማጠቃለያ (Executive Summery)፣ በክፍል አንድ- መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ መነሻ ችግሮች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ በጥናቱ መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች፣ በክፍል ሁለት- የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ስልት/ዘዴ (የጥናቱ ዓይነት፣ የጥናቱ ተሳታፊዎች፣ የጥናቱ መረጃ ምንጮች)፣ በክፍል ሶስት-የጥናቱ ትንተና /በሰነድ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ ከተሰባሰቡ መረጃዎችና ማስረጃዎች በመነሳት ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዙ የአሰራር፣ የግልፅነት፣ የሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት ያለባቸውን ጉዳዮች ለእያንዳንዱ ርዕስ በመስጠትና ትንተና በማድረግ አሰራሩን ከሙስናና ብልሹ አሰራር አኳያ የሚዳሰስበት ክፍል ማለት ነው፡፡ በክፍል አራት- የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች፣ የጥናቱ ምክረ-ሐሳብ እና የክትትልና ድጋፍ ስልቶች እና የማጠቃለያ ኃሳቦች የሚመላከቱበት ነው፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በአንድ ዘርፍ/ተቋም ውስጥ የሥራ ሂደቶች ግልጽ እንዳልሆኑ እና ለሙስና እድል እንደሚፈጥሩ ብታገኙ ምን እርምጃ ትወስዳላችሁ?

**አቶ ገዛኸኝ ጋሻው፡-** የሙስና መከላከል ጥናት በተጠኚ ዘርፍ (ተቋም) የሚደረግብት ዋናኛ ዓላማ የአሰራር ስርዓት እንዲሻሻል፣ ግልፅነት እንዲኖረው የማድረግ ሲሆን፣ በግልፅ የሕግ ጥሰት ተፈፅሞ ሲገኝ ደግሞ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡ ስለሆነም ባለፉት ጊዚያት በዚህ ዓመትም የተከናወኑ ጥናቶች የተለያዩ የአሰራር፣ የአደረጃጀት እና የሕግ ማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ተደርጓል፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በሙስና መከላከል ጥናት ሂደት ውስጥ የአስተዳደር አካላት/የተቋማት ኃላፊዎች ሚና ምንድን ነው ትብብር ባይኖርስ እንዴት ትሰራላችሁ?

**አቶ ገዛኸኝ ጋሻው፡-** የማንኛውም ዘርፍ ወይም ተቋም የበላይ ኃላፊ ዋነኛ ኃላፊነት ከሆኑት አንዱ በሚመሩት ተቋም ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መዋጋት፣ አሰራርን ግልፅ ማድረግ እና ሙስና ተፈፅሞ ሲገኝም የሕግ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ኮሚሽኑም ሆነ በዘርፍ እና ተጠሪ ተቋማት የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የሙስና መከላከል ጥናት በሚደረግበት ወቅት መረጃና ማስረጃዎች እንዲቀርቡና ጥናቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚህ ረገድ ከተቋማት ጋር በትብብርና በቅንጅት የጥናት ስራዎችን እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ትብብርና ቅንጅቱም ጥሩ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይሁንና በተቃራኒው ለጥናት ስራ አለመተባበር ቢኖር በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 22 መሠረት ኮሚሽኑ በአዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል ማለት ነው፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በጥናት የተለዩ ግኝቶች ለማረም የሚያስችሉ የጥናት ምክረ-ሀሳቦች ተግባራዊ ስለመሆናቸው እንዴት ትከታተላላችሁ?

**አቶ ገዛኸኝ ጋሻው፡-** የሙስና መከላከል ጥናቶች ተጠንተው ካለቁና ኮሚሽኑ ለተጠኚ ተቋማት ውይይት እንዲቀርብ አቅጣጫ ካስቀመጠ በኂላ ጥናቶቹ ለተቋማት ቀርበው ውይይት ይደረግባቸዋል፡፡ የጋራ ስምምነት ላይ እንዲደረስ ይደረጋል፡፡ ይህን ተከትሎ በጥናቱ የተለዩ ዋና ዋና ግኝቶችን መሠረት ያደረገ የምክረ ኃሳቦች መተግበሪያ የድርጊት መርሃግብር በማዘጋጀት ለኮሚሽኑ እንዲልኩ ለተቋማት ይላካል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ ምክረ ኃሳብ ምን ተሻሻለ፣ ምን ቀረ በሚል የጥናቱ ክትትልና የትግበራ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ኮሚሽኑ ያቀረበውን የማሻሻያ ምክረ ኃሳብ ተፈፃሚ የማያደርግ ተጠኚ ተቋም ካለም በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7(3) መሰረት ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

**የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በመጨረሻም ቀረ የሚሉት እና የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ መጨመር ይችላሉ፡፡

አቶ ገዛኸኝ ጋሻው፡- ሙስናና ብልሹ አሰራር በአንድ ተቋም ተጀምሮ በአንድ ተቋም የሚጠናቀቅ ተግባር አይደለም፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና ዜጎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት እስከአሁን ካደረጉት ተሳትፎ በበለጠ ሁኔታ የፀረ-ሙስና ትግላቸውን አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፤ ይኖርብናል እላለሁ፡፡

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA


# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

ለህብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
EARS



## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

NCRS


## ርዕሰ -አንቀፅ

# የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ፣ ዛፍ መትከል እና የሥነምህዳር መስተጋብር የህይወት ቀጣይነት ስንሰለት!

የሰው ልጅ በዚህች ምድር ላይ ሲኖር አካባቢውን የመንከባከብና የመጠበቅ ታላቅ አደራና ሀላፊነት አለበት:: ትውልድን ሥነምግባር እና ዛፍ መትከል የውስጥ ማንነት መገለጫ ናቸው፤ ከዚህ አንፃር ሥነምግባር ለአንድ ማህበረሰብ ወይም ለዓለም መልካም የሆነውን ነገር የማወቅ እና የመተግበር እሴት ነው:: ዛፍ መትከል ተራ የተፈጥሮ ስራ ሳይሆን ጥልቅ የሆነ የሥነምግባር መግለጫ ነው:: አንድ ሰው ዛፍ ሲተክል፣ ከራሱ ባለፈ ለወደፊቱ ትውልድና ለሌሎች ህያው ፍጥረታት እንደሚያስብ ያሳያል:: ዛሬ የሚተከል ዛፍ ነገ ለልጅ ልጆች ጥላ፣ ምግብና ንጹህ አየር እንደሚሆን ማሰብ የላቀ የሞራል ብስለት ነው:: የምስጋና እና የክፍያ እሴት ላይ ሰው ከተፈጥሮ በነፃ የሚያገኘውን አየርና ውሃ ሲጠቀም ይኖራል:: ዛፍ መትከል ለተፈጥሮ የምንከፍለው የምስጋና እዳ (የሞራል ግዴታ) ነው::

የሥነምህዳር ሚና እና ትስስር ስንመለከት ስነምህዳር በህይወት ባላቸው ፍጥረታት (ሰዎች፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት) እና ህይወት በሌላቸው ነገሮች (አፈር፣ አየር፣ ውሃ) መካከል ያለውን የተመጣጠነ መስተጋብር የሚገልጽ ሥርዓት ነው:: ዛፎች የዚህ ሥርዓት ልብ ናቸው:: ከህይወት ደጋፊነት አንፃር ዛፎች ካርቦንዳይኦክሳይድን በመምጠጥ ኦክስጅንን ያመርታሉ:: ይህ ደግሞ በምድር ላይ ያለውን የአየር ንብረት ሚዛን ይጠብቃል:: በአንድ ዛፍ ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ አእዋፋት፣ ነፍሳትና ጥቃቅን ህዋሳት ይኖራሉ:: ዛፍ መትከል ማለት ለእነዚህ ሁሉ ፍጥረታት ህልውና መፈጠር ማለት ነው:: የዛፍ ስሮች አፈርን አጥብቀው በመያዝ የአፈር መሸርሸርን ይከላከላሉ፤ የከርሰ ምድር ውሃ እንዲጨምርም ያደርጋሉ:: ሥነምግባር እና ስነምህዳር በዛፍ መትከል አማካኝነት ወሳኝ ዝምድናዎች ይፈጥራሉ::

በየአካባቢው ሥነምግባር መፈጠር ተፈጥሮን አለማጥፋት ብቻ ሳይሆን፣ የተጎዳውን መልሶ ማልማት የሰው ልጅ የሞራል ግዴታ መሆኑን ያሳያል:: ዛፍ መትከል ይህንን ሥነምግባራዊ እሴት በተግባር የምናሳይበት መንገድ ነው:: ሥነምግባር የጎደለው የሰው ልጅ ስግብግብነት (ዛፎችን መጨፍጨፍ፣ አካባቢን መበከል) ስነምህዳሩን ያናጋዋል:: በአንጻሩ፣ ሥነምግባራዊ አስተሳሰብ ሲኖር ዛፎችን በመትከል የተናጋውን የስነምህዳር ሚዛን መልሶ ማስተካከል ይቻላል:: ዛፍ መትከል "እኔ ከኖርኩ ሌላው ቢጠፋ ግድ የለኝም" የሚለውን ራስ ወዳድነት ሰብሮ፣ "ሁላችንም በጋራ ስንኖር ነው መኖር የምንችለው" የሚለውን የስነምህዳር እውነት ያጸናል:: የዘንድሮው የችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር "ተስፋን እንትከል" በሚል መሪ ቃል በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ፒ.ኤች.ዲ) በይፋ ተበስሯል::

በአጠቃላይ ዛፍ መትከል የአፈር መቆፈር እና ችግኝ የመትከል ተግባር ብቻ አይደለም:: እሱ የሰው ልጅ የውስጥ መልካም ሥነምግባር ፍሬ አፍርቶ ውጫዊውን ስነምህዳር የሚፈውስበት ጥበብ ነው:: እያንዳንዱ የምንተክለው ዛፍ ለተፈጥሮ ያለንን አክብሮት፣ ለትውልድ ያለንን ፍቅር እና ለምድር ህልውና ያለንን ታማኝነት የምናሳይበት ህያው ምስክር ነው:: ስለዚህ፣ አረንጓዴ አሻራን ማሳረፍ የላቀ ሥነምግባርና የተስተካከለ ስነምህዳር ለመገንባት ዋነኛው መፍትሄ በመሆኑ ሁላችንም ዛፍ በመትከል የትውልድ አደራችንን ልንወጣ ይገባል::

# ሳይቃጠል በቅጠል

## ሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) ሙስናን ለመከላከል ያለው ፋይዳ የጎላ ነው!

ሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገራችን ኢትዮጵያ ሙስናን ለመከላከል፣ ለማጋለጥ እና ግልጽነትን ለማስፈን ትልቅ አቅም ይዞ የመጣ የቴክኖሎጂ መሳሪያ ነው። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በማደግ ላይ ያሉ፣ የመንግስትን አሰራር ዘመናዊ ለማድረግ እና የሰዎችን አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ለመቀነስ ለሚደክሙ ሀገራት ሰው ሰራሽ አስተውሎት(AI) ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ሀገራችን አሁን ላይ ከጀመረችው የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ አንጻር፣ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ሙስናን ለመከላከል ያላቸው ዋና ዋና ፋይዳዎች እና በኢትዮጵያ አውድ ሊተገበሩ የሚችሉባቸው መንገዶች የሚከተሉት አምስት ዋና ዋና ነጥቦች ተጠቃሽ ናቸው።

የፋይናንስ ፍሰትን መከታተል እና ያልተለመዱ ነገሮችን መለየት፣

ባህላዊ የኦዲት አሰራር ሙስና ከተፈጸመና ገንዘቡ ከጠፋ ከረዥም ጊዜ በኋላ ስህተቶችን ያገኛል። ሰው ሰራሽ አስተውሎት(AI) ግን በሚሊዮን የሚቆጠሩ የባንክ እና የፋይናንስ ግብይቶችን በሰከንዶች ውስጥ መተንተን ይችላል። በተለይ ያልተለመዱ ዝውውሮችን መለየት ይቻላል። ከአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት አካውንት ወደ ግል ግለሰቦች አካውንት የሚደረጉ ያልተለመዱ እና የባንክ አሰራርን ያልተከተሉ የገንዘብ ፍሰቶችን ወዲያውኑ ይጠቁማል።

ቀይ መስመር ስርዓት አለው፤ ህጋዊ ካልሆኑ የሀብት ማከማቸቶች እና ከወንጀል የተገኘ ገንዘብን ህጋዊ ከማስመሰል ጋር የተያያዙ ጥርጣሬዎችን በቅጽበት በመለየት ለቁጥጥር አካላት ጥቆማ ይሰጣል። ለአብነት በአንድ ባንክ ላይ የገንዘብ ዝውውር ስርዓት ላይ የAI አልጎሪዝም ቢገጠም፣ በአንድ የመንግስት ፕሮጀክት ማግስት የአንድ መካከለኛ የመንግስት ሰራተኛ ወይም የቅርብ ዘመዱ አካውንት ላይ በድንገት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ብሮች ሲገቡና ሲወጡ ስርዓቱ ወዲያውኑ የማስጠንቀቂያ ምልክት በማሳየት ለሚመለከተው አካል መረጃ ማስተላለፍ ይችላል።

በግዥ እና ጨረታ ሂደት ውስጥ ግልጽነትን ይፈጥራል፤ የመንግስት ግዥ እና ጨረታ (Procurement) በሀገራችን ለከፍተኛ ሙስና እና ለህዝብ ሀብት ብክነት በጣም ከተጋለጡ ዘርፎች ቀዳሚው ነው። AI በዚህ ረገድ የሚከተሉትን ያደርጋል። ከጥቅም ግጭትን ማጋለጥ አንፃር ሲታይ፤ የጨረታ አሸናፊዎችን የባለቤትነት መረጃ ከባለስልጣናት ወይም ከግዥ ኮሚቴ የቤተሰብ እና የጥቅም ትስስር ጋር በማነጻጸር የጥቅም ግጭት ካለ በራሱ አባላት ይለያል። የዋጋ ማጭበርበርን ይከላከላል። የቀረቡ የጨረታ ዋጋዎችን ከአለም አቀፍ እና ከአገር ውስጥ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጋር በማነጻጸር ዋጋ የተጋነነባቸውን ግዢዎች ውድቅ ያደርጋል።

የመመሳጠር ጥርጣሬዎችን ማግኘት ይችላል፤ የተለያዩ ድርጅቶች ተመሳጥረው ጨረታውን ለመቀራመት ዋጋ አቀራረባቸውን ወይም የሰነድ አዘገጃጀታቸውን አንድ አይነት ካደረጉ AI ይህንን ሴራ በቀላሉ ይደርስበታል። ለአብነት በመንግስት የግዥና ንብረት ባለስልጣን ስር አሁን ባለው የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት (e-GP) ላይ AI ቢተገበር፣ ለአንድ ክፍለ ከተማ መንገድ ግንባታ ወይም ለትምህርት ቤት ግብዓት ግዥ የቀረቡ የሶስት የተለያዩ ድርጅቶች የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዶች የፊደል ስህተት ሳይቀር ተመሳሳይ መሆኑን፣ ወይም የገበያ ዋጋው 50 ብር የሆነን እቃ 500 ብር ተብሎ መቅረቡን ፈልፍሎ በማውጣት ጨረታው በሰው ጣልቃገብነት እንዳይጸድቅ ያግዳል።

የሰዎችን ጣልቃ ገብነት መቀነስ እና አገልግሎትን ዲጂታላይዝ ማድረግ ይገባል፤ ለሙስና መፈጠር አንዱ ትልቅ ምክንያት የአገልግሎት ፈላጊው ህዝብ እና የአገልግሎት ሰጪው በአካል በቀጥታ መገናኘታቸው ነው። አገልግሎቶች በAI እና በዲጂታል ስርዓት ብቻ ሲመሩ፣ የሰራተኞች ሆን ብሎ ማመልከቻን የማዘግየት፣ የመደለል ወይም ጉቦ የመጠየቅ ዕድል ይጠፋል። ግልጽ መስፈርቶች አሉት፤ ማመልከቻዎች በሰው ፍላጎት ወይም ትውውቅ ሳይሆን በAI መስፈርት ብቻ ስለሚገመገሙ አድልዎ ይወገዳል። ለአብነት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማስተዳደር ቢሮ ወይም በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ፈቃድና እድሳት ላይ የAI ስርዓት ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ቢውል። አንድ ግለሰብ የይዞታ ማረጋገጫ (ካርታ) ለማውጣት ወይም ለማደስ ሲጠይቅ፣ ማመልከቻው በAI አማካኝነት ከዲጂታል ማህደሩ ጋር ተገናኝቶ መስፈርቱን ካሟላ በደቂቃዎች ውስጥ ውሳኔ ያገኛል። ይሄ ሲሆን "ዛሬ ኃላፊው የለም፣ ነገ ኑ፣ ፋይልህ ጠፍቷል" የሚሉ የጉቦ ማግኛ ሰበቦች ሙሉ በሙሉ ይከስማሉ።

የሀብት ምዝገባ እና የስጋት ትንተና፡ - የመንግስት የስራ ኃላፊዎችን እና ባለስልጣናትን ሀብት የመመዝገብ እና የመቆጣጠር ሂደትን AI እጅግ ቀልጣፋ እና እውነተኛ ያደርገዋል። የሀብት እና የገቢ አለመመጣጠንን መለየትም ያስችላል፤ የአንድ ባለስልጣን ህጋዊ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም በባንክ ካለው የገንዘብ ዝውውር ወይም በስሙ/በቤተሰቡ ስም ከተመዘገበ ንብረት ጋር የማይመጣጠን ከሆነ ስርዓቱ ወዲያውኑ ጥርጣሬ ያመነጫል።

ከደረጃ ስጋት አንፃርም ሲንመለከት፤ ለሙስና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ መሥሪያ ቤቶችን (ለምሳሌ፦ ጉምሩክ፣ ታክስ፣ መሬት) እና የስራ መደቦችን በመለየት የክትትል ትኩረት እንዲደረግባቸው ያግዛል። ለአብነት በጉምሩክ ኮሚሽን ወይም በገቢዎች ሚኒስቴር ውስጥ የሚሰራ የአንድ መካከለኛ ደረጃ ያለው ሰራተኛ ወርሃዊ ደሞዝ እየታወቀ፣ AI ግን ከተለያዩ ተያያዥ የመረጃ ቋቶች (የቤትና መኪና ምዝገባ ማህደር) በመነሳት በቅርብ ጊዜ በባለስልጣኑ ወይም በቅርብ የቤተሰብ አባላቱ ስም በጄሞ ወይም በአየር ጤና አካባቢ የተገዙ ውድ ህንፃዎችን ወይም ተሽከርካሪዎችን በማጣቀስ "ይህ ሀብት ከህጋዊ ገቢው ጋር አይመጥንም" የሚል የስጋት ደረጃ ለቁጥጥር አካላት ይሰጣል።

የጥቆማዎችን ትክክለኛነት ማጣራት፡- የፀረ-ሙስና ተቋማት ከህዝብ በርካታ የሙስና ጥቆማዎች በስልክ፣ በደብዳቤና በድረ-ገጽ ይደርሷቸዋል። ሁሉንም ጥቆማዎች በሰው ኃይል ብቻ አንድ በአንድ ማጣራት ጊዜና ወጪ ይጠይቃል። የደረሱትን ጥቆማዎች የቃላትና የይዘት ትንተና በማድረግ፣ ጠንካራና እውነተኛ ማስረጃ ያላቸውን እና ስም ማጥፋት ወይም በቀል የሆኑትን በመለየት ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ መዝገቦችን ለኮሚሽኑ ሰራተኞች ያዘጋጃል። ለአብነት የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይፋዊ የጥቆማ መቀበያ የዲጂታል መተግበሪያ ሥርዓት (NCRS)) ወይም የስልክ መስመር አለው። AI በየቀኑ የሚመጡትን በሺዎች የሚቆጠሩ ጥቆማዎችን ያነባል/ያዳምጣል። ለምሳሌ በአንድ የክልል ተቋም ውስጥ "የእርዳታ እህል እየተመዘበረ ነው" የሚል ጥቆማ በተደጋጋሚ በተለያዩ ሰዎች ከተላከ፣ AI ይህንን አዝማሚያ በፍጥነት በመረዳት ለጉዳዩ 90% የዕውነትነት ደረጃ በመስጠት አጥኚዎች ወዲያውኑ ወደ ስፍራው እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል።

ወደፊት ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፣

የሰው ሰራሽ አስተውሎት (AI) በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል ውስጥ ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ቢሆንም፣ ቴክኖሎጂው በራሱ ተዓምር ሊፈጥር አይችልም። ሙሉ በሙሉ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ቅድመ-ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው። የባንኮች፣ የገቢዎች (ታክስ)፣ የንግድ ፈቃድ እና የንብረት ምዝገባ የዲጂታል መረጃዎች እርስ በርስ መገናኘት አለባቸው። እንዲሁም ወደ ስርዓቱ የሚገባው መረጃ የተሟላና ከስህተት የጸዳ መሆን አለበት። የAI ቴክኖሎጂውን የሚመሩት አካላትና ተቋማት ራሳቸው ገለልተኛ፣ ታማኝና በህግ ተጠያቂነት ያለባቸው መሆን ይኖርባቸዋል። በአጠቃላይ፣ AIን በፀረ-ሙስና ትግሉ ውስጥ በአግባቡ መጠቀም መቻል የሀገርን ሃብት ከብክነት ከማዳኑም በላይ ህዝቡ በመንግስት አሰራር ላይ ያለው እምነት ከፍ እንዲል ያደርጋል።

## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት እንዲሁም ሀገራችን ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው::

በመሆኑም፣ በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ግለሰብ በ 2 አመት ከ9 ወር ፅኑ እስራት እና 56,000 ብር እንዲቀጣ ተወስኗል:: ተከሳሽ አቡሽ ዘውዱ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሚያዚያ 30 ቀን 2017 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 5:00 ሰዓት አካባቢ ጎንደር ከተማ ቀበሌ 11 ልዩ ቦታው ጃንተከል ክፍለ ከተማ በታክሲ ተሳፍሮ እየሄደ እያለ ፍተሻ ሲደረግ



ስራውን በለቀቀ ግርማ ነጋ በሚባለው ከሶስት ዓመት በፊት የጃንተከል ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጽ/ቤት በነበረ ኃላፊ ስምና ፊርማ 1ኛ በቁጥር ጃንተከል ክፍለ ከተማ 109 በቀን 14/04/2017 ክላሽ መሳሪያ ፍሬም ቁጥሩ 1503 ከመሰል 90 ጥይት ጋር ከ15/04/2017 እስከ 15/06/2017 ዓ.ም እንዲያገለግል የተፃፈ ጊዜያዊ የይለፍ ደብዳቤ፤

2ኛ ከላይ ለተጠቀሰው መሳሪያና ጥይት በቁጥር ጃንተከል ክፍለ ከተማ 209 ከ01/08/2017 እስከ 01/10/2017 እንዲያገለግል የተፃፈ ሁለት ጊዜያዊ የይለፍ /ወረቀት/ደብዳቤ ይዞ ህጋዊ ነኝ በሚል ሀሰተኛ የይለፍ ሰነዶችን በማሰየት ሲገለገልበት ተገኝቷል በሚል የጎንደር ከተማ አስተዳደር 2ኛ ዋና ፖሊስ ጣቢያ አጣርቶ ያቀረበለትን የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ የፀረ-ሙስና የስራ ሂደት የፀረ-ሙስና አዋጁ 881/07 አንቀፅ 23(3)ን ጠቅሶ ክስ ለማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል::

ተከሳሽም በተከሰሰበት ድንጋጌ ተከላከል ከተባለ በኋላ ተደጋጋሚ ቀጠሮ ተሰጥቶት የቀረ ሲሆን፣ በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 20 መሰረት የተሰጠውን የተከሳሽነት መብት ተጠቅሞ ተከላከል ከተባለ በኋላ የቀረ በመሆኑ ፍ/ቤቱ መዝገቡን መርምሮ በዋለው ችሎት 2 አመት ከ9 ወር ፅኑ እስራትና 1000 ብር ወስኗል:: ዐቃቤ ህግም በቅጣት አስተያየት ጊዜ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/07 አንቀፅ 7 ከፍትህ ማምለጥ ወንጀል የተሟላ በመሆኑ በተደራቢነት ከሚፈረድበት ላይ በድንጋጌው መሰረት ተከሳሽ እንዲቀጣ ያሳሰበ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የተፈረደበትን ፍርድ/ቅጣት ከግምት ውስጥ በማስገባት የድንጋጌውን መነሻ ቅጣት 20,000 ብር በመያዝ 55,000 ሺ ብር በተጨማሪ እንዲቀጣ ወስኗል:: ተከሳሽን አፈላልጎ በመያዝ ለጎንደር ማ/ቤት እንዲያስረክብ ለፖሊስ ጣቢያ ትዕዛዝ ተሰጧል::

## መልካም ዜጋ

### አበበች ጎበና: የኢትዮጵያዋ “እናት ቴሬዛ!”

እናት አበበች ጎበና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በደግነታቸው፣ በምህረታቸውና ለሰው ልጆች ባላቸው ጥልቅ ፍቅር የማይረሳ መልካም አሻራ ጥለው ያለፉ የሰብዓዊነት ተምሳሌት ናቸው:: እሳቸው ለብዙ ሺህ ህጻናት ተስፋ፣ መጠለያና ህይወት የሆኑ ድንቅ እናት ነበሩ:: የእናት አበበች የሰብዓዊነት ስራ የተጀመረው በ1970ዎቹ አጋማሽ በኢትዮጵያ ተከስቶ በነበረው አስከፊ ድርቅ ወቅት ነበር:: በወቅቱ ወደ ግሽን ማርያም ለንግሥ በሄዱበት ወቅት፣ በረሃብ ምክንያት ህይወቷ ካለፈ እናት ጎን ተኝታ ጡት የምትጥባትን ህጻን ሲመለከቱ ልባቸው በሀዘን ተነካ:: ያቺን ህጻንና ሌላም አንድ ህጻን ይዘው ወደ አዲስ አበባ በመመለስ የዛሬው “አጎሄልዳ” (AGO-HELMA) መሰረት የሆነውን የበጎ አድራጎት ስራ በቤታቸው ጀመሩ::



እናት አበበች ይህንን የተቀደሰ አላማ ለማሳካት የግል ምኞታቸውንና የትዳር ህይወታቸውን ጭምር መስዋዕት አድርገዋል:: በወቅቱ የነበራቸውን ጥቂት የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን በመሸጥና ህጻናቱን መመገብ ጀመሩ:: “የኔ” ሳይሉ ለሰው ልጆች መኖርን መመሪያቸው አድርገው ለዘመናት ጸንተዋል:: ርህራሄ ለማያውቋቸውና ዘመድ ለሌላቸው ህጻናት የገዛ እናታቸው በመሆን ፍቅርን ሰጥተዋል:: ካለ ምንም ትልቅ የገንዘብ ድጋፍ ስራቸውን በራሳቸው ጥረት ጀምረው፣ ዛሬ በሺዎች የሚቆጠሩ ህጻናት የሚረዱበት ትልቅ ተቋም ገንብተዋል:: ሴቶች በራሳቸው ጥረት ማህበረሰባቸውን እንዴት መለወጥ እንደሚችሉ በተግባር አሳይተዋል::

በበጎ ሥራዎቻቸው እውቅናን ያተረፉት እና ‘የአፍሪካዋ ማዘር ትሬዛ’ በሚል ስያሜ የሚታወቁት የክብር ዶክተር አበበች ነፍሳቸው ከስጋቸው ቢለያይም በህይወት ዘመናቸው ባከናወኑት ተግባር በርካታ አገር አቀፍና ዓለምአቀፍ ሽልማቶችን አግኝተዋል:: ሆኖም ለእሳቸው ትልቁ ሽልማት የዳኑት ህጻናትና ዛሬ ላይ ደርሰው አገር የሚጠቅሙ ዜጎች መሆናቸው ነበር:: እናት አበበች “መልካምነት ለራስ ነው” የሚለውን ብሂል በተግባር ያሳዩ፣ የፍቅርና የርህራሄ መምህር ነበሩ:: በመልካም ሥራዎቻቸው



# ኪነ-ጥበብ

## ሥነምግባር

### ሙስና ይወገዝ...!

የእድገት ጎዳና ጎታች ወደኋላ፣
ተስፋን አጨላሚ የዘመን አሽካላ፡፡
ክፉ የሀገር ጠንቅ የወገን ነቀርሳ፣
ሙስና ይወገዝ ከሃገር ይነሳ፡፡
መገለጫው ብዙ ሰፊነው ምህዳሩ፣
አንዳንዴም በልማድ ያደርጋል አጋሩ፡፡
እየሳበ ሰውን ልክ እንደሚሰራ፣
ነገሮችን ሁሉ አስመስሎ ተራ፡፡
ሰዓት ያለማክበር ሙስና ማይመስለው፣
ደረቱን ገልብጦ ቢሮ የሚገባው፡፡
ከዚያም ጥቂት ሳይቆይ ትንሽም ሳይሰራ፣
ስራ ተቆልሎ ልክ እንደተራራ፣
ሻይ ቡና ብሎ ከመሰሉ ጋራ፣
ይወጣል ከቢሮው ይሉኝታን ሳይፈራ፡፡
ይሄን ተመልክቶ ይከተላል ሌላው፣
በዚህም በዚያኛው ይበደላል ስራው፡፡
ለምን እማራለሁ ለምን እደክማለሁ፣
በእድገትና ቅጥሩ አድሎውን እያየሁ፣
ለማን ብዬ ደግሞ ተግቼ እሰራለሁ፣
ሌላው ዘና እያለ ለምን እጎብጣለሁ፣
አፋጣኝ ውሳኔን በቃ እጎትታለሁ፣
እጅ መንሻ ሲሰጠኝ ያኔ አሳልፋለሁ፡፡
ህገወጥነት ለምን እታገላለው፣
ሸጎጥ ካረገልኝ አይቼ እንዳላየ ዝም ብየው አልፋለሁ፣
ባፀፋው ጉርሻዬን በደንብ አገኛለሁ፡፡
ብዬ መለስ ስል ኪሴን ከሞላልኝ፣
ገቢ ገባ አልገባ እኔን ምን ቸገረኝ፡፡
ገዝቼ አስገባለሁ ምራጭ የወደቀ፣
ኮሚሽን ካገኘሁ አለቀ ደቀቀ፡፡
ሙስና እያደር ግዛቱ ሲሰፋ፣
ይባላል የመሬት ማህደሩ ጠፋ፡፡
ሌላውም ሌላውም ሁሉም በየዘርፉ፣
በእንዲህ አይነት መንገድ ሀገርን ዘረፉ፡፡
የተቋማት ታሪክ እውነታው ይሄ ነው፣
ለሙስና ቤቱ ዘርፉ የበዛ ነው፡፡
እንዳልሆነ ሆኖ ኖረ ብዙ ዘመን፣
እዚያው ሲልወሰወስ ሳያሳይ እድገቱን፡፡
አሁን ግን ጊዜው የሙስና ትግል ጊዜው በመሆኑ፣
ከላይ የተባሉት ድርጊት በሙሉ፣
በጽኑ ቁጥጥር በትግል ይጠፋሉ፡፡
ሙስናን እናውግዝ ሆነን በአንድ ላይ፣
ከዚህ የበለጠ ብዙ እድገት እንድናይ፡፡

ከለምለም ጥበቡ